## መጽሐፈ ሩት 1፡1-22

በመሳፍንት ዘመን በእስራኤል ምድር ረሀብ ሆነ። በዚህ ዘመን የነበረው ትውልድ ምን ዓይነት እንደነበረ ለመጥቀስ ያህል፡-

እግዚአብሔርም ሆነ እርሱ ለእስራኤል ህዝብ ያደረገውን ነገር የማያውቅ ሌላ ትውልድ ተነሳ፣ በእግዚአብሔር ፊት ካደረጋቸው ክፉ ነገሮች መካከል የሚከተሉትን ይገኙበታል።

- የአካባቢው ህዝብ የሚያመልካቸውን ጣዖታት አመለኩ፡ ካሞሽ..... የሞአባዊያን፣ ሞሎክ....የአሞናውያን፣ ባአሊምና አስታሮት..... የከነአናውያን/የሲዶናውያን አማልክት ነበሩ።
- ጣኦታት ማምለካቸው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ጸያፍ የሆኑ የኀጢአት ድርጊቶች ፈጸሙ .... ዝሙት.... በዙሪያቸው ያሉት አህዛብ ሴቶችን አገቡ። የነርሱም ሴት ልጆች ለአህዛብ ዳሩ/ሰጡ።
- ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣቸውን እግዚአብሔርን ማምለክ ተዉ።
- በዚህ ምክንያት አግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ይቀጣቸው ነበር (በጦርነት መጨነቅ፣ በድርቅ፣ በረሀብ...)
- መከራ እጅግ ሲበዛባቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሁና እግዚአብሔርም ታዳጊ ያስነሳላቸው ነበር።
- ያ አግዚአብሔርር ያስነሳላቸው ታዳጊ መስፍን ሲሞት መልሰው ወዳለፈው አይነት የተበላሸ አካሄድ ይመለሱ ነበር። የሚተላለፉት የእግዚአብሔር ስርዓት የእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት እንደ ሚያስከትልባቸው ቢያውቁም የእልከኝነት መንገዳቸውን አይተውም ነበር።

**የሩት መጽሐፍ ምእራፍ አንድ ታሪክ ተዋናዮችና በሄዱበት አገር የገጠማቸው ሁኔታ ሲታይ፡-**

የተሰደዱት ወደ ሞአባውያን ምድር ነበር። ዘፍ 19፡30-38፣ ሎጥ የአብርሐም ወንድም ልጅ ነው። የሎጥ ታላቅ ሴት ልጅ የወለደችው ሞአብ የሞአባውያን አባት ነው። ታናሺቱ የወለደችው ቤንአሚ ሲሆን እርሱ የአሞናውያን አባት ነው። በመሳፍንት ዘመን እስራኤልን እጅግ ካስጨነቁ የአካባቢው ነገስታት አንዱ የሆነው ንጉስ ኤግሎን ሞአባዊ ነበር። ግራኙ ናዖድ ከእስራኤል የተሰበሰበ ግብር ለንጉስ ኤግሎን ሊከፍል ሄዶ የምነግርህ ምስጢር አለኝ ብሎ በማታለል ከነጉሱ ጋር የነበሩት የክብር ዘቦች ሲወጡለት ልብሱ ውስጥ የደበቀው ሰይፍ መዝዞ 18 ዓመት ያስጨነቃቸው ሞዓባዊውን ንጉስ ገደለው።

አብርሐምና የወንድሙ ልጅ ሎጥ እንዲህ የቅርብ ዘመዶች ሆነው ሳለ ከጊዜ ብዛት የተነሳ ተባዝተው ብዙ ሕዝብ ሲሆኑ ዝምድናው ተረስቶ አንዱ ሌላውን ለመግዛት ጦር ተማዘው ተላልቀዋል። (መሳ 3፡12-25) የኑኃሚን ቤተሰብ ወደ ሞአብ ምድር በተሰደደ ጊዜ ግን በሁለቱ ወገኖች በኩል አንጻራዊ ሰላም እንደነበረ ይነገራል። እኛም ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በመሳፍንት ዘመን አካባቢ የነበረ ታሪካችን በጽሁፍ የሰፈረ ስሌለና ስለተባዛን ነው እንጂ ልክ እንደ እስራኤላዊያንና ሞአባዊያን የቅርብ ዘመዳሞች መሆናችንን ተገንዝበን እርስ በርስ መዋጋታችንን አቁመን ለጋራ ጥቅማችን ተባብረን መስራት ይኖርብናል።

አቤሜሌክ የተባለው የኑኅሚን ባለቤት በወቅቱ በእስራኤል የተከሰተው ረሀብ መቋቋም ስላልቻለ ሁለት ልጆቹንና ባለቤቱን ይዞ ወደ ሞአብ ምድር ተሰደደ፡፡ የኑኃሚን ባል እዚያው ሞተ፡፡

የኑኅሚን ልጆች ሞአባዊያን ሴቶችን (ሩትና ኦርፋ የሚባሉ) አግብተው መኖር ጀመሩ፡፡ በተለያየ አካባቢ የኖረ ሰው በጋብቻ ተገናኝቶ አብሮ መኖር ሲጀምር አንዱ ወገን ባህሉን፣ አመለካከቱን፣ እውቀቱን፣ እምነቱን፣ ሞያውን ለሌላው ወገን ማናጸባረቁ/መግለጡ አይቀርም፡፡ እግዚአብሔር ከአህዛብ ጋር እንዳይጋቡ ያዘዛቸው በዚህ ሁኔታ የእነርሱን አማልክት መከተል እንዳይማሩ ነበር፡፡

- ስለዚህ እነ ሩት በአካባቢያቸው ስለ ሚመለኩት ካሞሽና ሞሎክ፤ ስለሚባሉት አማልክት በተለያየ ምክንያት በማንሳት መናገራቸው አይቀርም፡፡ በምላሹ ኑኃሚንና ልጆችዋም ስለ እስራኤል አምላክ ማንነት መናገራቸው ስለማይቀር አንዱ ወገን ለሌላው ወገን የአማልክቱን ችሎታና ዝና ሲያሰማ የኑኃሚን ወገኖች አምላካቸው ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እጅግ ብዙ ድንቅ ሥራዎች የሰራ በመሆኑ ከሰራው ታላቅ ሥራ ጥቂቱን እንኳ ከተናገሩ እነ ሩት በጣም እንደ ሚደነቁበት መገመት ይቻላል፡፡
- አንዱ ወገን ለሌላው በማህበራዊ ኑሮ የሚያሳየው ባህርይ... ከምእራፉ መረዳት እንደሚቻለው ሩትና ኦርፋ ባሎቻቸውና ኑኃሚን በባህርይ ባይመቹአቸውና ባይወዱዋቸው ኖሮ አብረንሽ ወዳገርሽ እንሂድ ባላሉም ነበር፡፡

እንዲህ ተግባብተው በመኖር ላይ ሳሉ የኑሃሚን ልጆች ሁለቱም ተራ በተራ ሞቱ፡፡

በህይወት የተረፉት የቤተሰቡ አባላት ለገጠማቸው የኑሮ ሁኔታ የሰጡት ምላሽ ይህን ይመስላል፤

1. **ኑኅሚን**፡- በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል በዙ ጊዜ የኖረችና ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ከፈለገች ብዙ ልታውቅ የምትችል ነበረች፡፡ ከአገሯም በረሀቡ ስትሰደድ ያልተሰደዱም ይኖራሉ፡፡ ከአገሯ ይዛ የወጣቻውን ባልዋና ልጆችዋን ተራ በተራ በማጣት ከባድ ሀዘን ደርሶባት ብቻዋን በሞአብ ምድር በመቅረቷ በከፍተኛ ሁኔታ ተከፍታለች፡፡
   ሩት 1፡6፣ እግዚአብሔር በተለያየ ኃጢአት አምላኩን ላሳዘነው ለእስራኤል ህዝብ ራርቶ እንደ ጎበኛቸውና ምግብ እንደሰጣቸው ስትሰማ ወዳገሯ ለመመለስ ወስና ጉዞ ጀምራለች፡ ፡ 1፡13፣ 20-21፣ ከንግግሯ እንደሚታየው ወዳገሯ ብትመለስም እንኳ ስለ ወደፊቱም ኑሮዋ ተስፋ ሁኔታ ቆርጣለች (ግን በእግዚአብሔር ተስፋ አይቆረጥም፡፡) ሰቆ 3፡26፣

   ለገጠማት ችግር የራስዋም ሆነ የባልዋና ልጆችዋ እንዲሁም የአገርዋ ሕዝብ ኃጢአት ስላለው አስተዋጽኦና **ንስሃ ጉዳይ** ምንም ስትናገር አይሰማም ፡፡ ነገር ግን አጥብቃ እግዚአብሔርን **ስታማርር** ይሰማል (ኑኅሚን ማለት- ደስታዬ ማለት ነው፣ ማራ ደገሞ- መራራ ማለት ነው፡፡)
   ሩት 1፥13፣ "...የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ተነሥቶአልና፡፡"
   ሩት 1፡20-21፣ እርሷም እንዲህ አለች፤ "ሁሉን የሚችል አምላክ ሕይወቴን እጅግ መራራ አድርጎታልና ማራ በሉኝ እንጂ፣ ኑኃሚን ብላችሁ አትጥሩኝ፡፡ 21 በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ፤ እግዚአብሔር አስጨንቆኝ፣ ሁሉን

የሚችል አምላክ መከራ አምጥቶብኝ ሳለ እንዴት ኑኃሚን ብላችሁ ትጠሩኛላችሁ?" አለቻቸው።

ይሄ ሁኔታ የደረሰባቸው ግን የእስራኤላዊያን አመፃ በእግዚአብሔር ላይ በበዛበት በመሳፍንት ዘመን ነበር። በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉስ አልነበረም። የሕዝቡ አኗኗር እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን በማድረግ የሚኖርበት ጊዜ ነበር። በብዙ መከራ ሲጨነቁ ወደ እግዚአብሔር ይጮሁ ነበር። እግዚአብሔርም ታዳጊ መሳፍንትን ተራ በተራ ያስነሳላቸው ነበር። እያንዳንዱ መስፍን በህይወት በነበረበት ዘመን እግዚአብሔርን ይከተሉ ነበር። መስፍኑ ሲሞት ግን እንደገና ወደ ኃጢአት ይመለሱ ነበር። (ሰው በራሱ ተላላነት ህይወቱን ያበላሻል፣ በልቡ ግን እግዚአብሔርን ያማርራል ይላል መጽሐፍ ቅዱስ፤ ምሳ 19፡3።)
**በተለያየ ችግር ውስጥ ያለን ብንኖር ራሳችንን መርምረን ንስሀ እንግባ እንጂ እግዚአብሔርን ማማረር /ማጉረምረም/በእርሱ ማመካኘት እንደሌለብን የሚያነቃ ነው።)**
አብረዋት የነበሩት ምራቶችዋን ከኔ ጋር ብትሄዱ ምንም ባል የማግኝትና ኑሯችሁ የሚሻሻልበት ተስፋ የለምና **ወደ አማልክቶቻችሁና ወገኖቻችሁ ሂዱ** ብላ ደጋግማ አጥብቃ ጠይቃለች። ይህን ያደረገችው ለነርሱ የተሻለ ነገር እንዲገጥማቸው በማሰብ ነው።

ከአገሯ ቤትዋን ለቃ ከወጣች አስር ኣመታት ያህል ስለሆነ መጠለያ ቤት የነበራት ቢሆን እንኳ አሁን ፈራርሶ የሚወድቅበት ጊዜ ነው። **በዚህ ዓለም ሳለን ምንም ያህል ችግር ቢገጥመን ሰዎች ከእግዚአብሔር ቤት እንዲርቁ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ መምከር ይሁንልን።**
እግዚአብሔር በምታገቡት ባሎቻችሁ ቤት ያሳርፋችሁ በማለት ትዳር ማረፊያ ቦታ እንደሆነ ተናግራለች (እንዲህ ዓይነት አባባል ላላገባች ሴት ልጅ በተለምዶ እኛም ሀገር የሚባል ቢሆንም እርሰ በርስ የሚገዳደሉ ተጋቢዎችም አሉ። **ለማንም ሰው እውነተኛና ሙሉ ማረፊያ የሚሆነው እግዚአብሔር ራሱ** ነው፣ ኢያ 23፡1፣ ኤር 6፡16፣ መንታ መንገድ ላይ ቁሙ፤ መልካሚን የጥንቷን መንገድ ጠይቁ፣ በእርሷም ሂዱ፣ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ። ማቴ 11፡28-29።)
"ከዚያም ኑኃሚን ሁለቱን ምራቶቿን እንዲህ አለቻቸው፤ "እያንዳንዳችሁ ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ፤ ለሞቱ ባሎቻችሁና ለእኔ በጎ ነገር እንዳደረጋችሁ፣ ለእናንተም እግዚአብሔር እንደዚሁ ያድርግላችሁ፤" ሩት 1፥8፣
ከላይ የሰፈረው ኑኅሚን የተናገረችው ቃል ሁለቱም መምራቶችዋ ባሎቻቸው ከሞቱ በኋላ የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ በፍቅር ይዘው የተንከባከቡዋት መሆኑን ያሳያል።

2. **ኦርፋ፡-** አብራ ወደ ኑኃሚን አምላክና ወገኖች ለመሄድ ጉዞ ጀምራ ሳለ ባል/የተሻለ ኑሮ የማግኘት ተስፋ እንደሌላት ስትነግራት ከኑኃሚና ከሩት መለየተዋን አሳዝኗት አልቅሳ ተሰናበተቻት። ስለ እስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሩት የሰማችውን ያህል ብትሰማም የተሻለ ኑሮ አገኝበታለሁ ወዳለችው ህዝብና ጣዖታት/አማልክት በገዛ እግሯ በራሷ ውሳኔ ሄደች እንጂ አማልክቱ ወደርሷ አልመጡም። ከዚያ በኋላ ከእስራኤል አምላክና

ከህዝቡ ጋር ሕብረት የማድረግ ዕድል ስለማግኘቷ በመጽሓፍ ቅዱስ ምንም አልተጠቀሰም።

3. ሩት፡- ኑኃሚን ተመለሺ ብላ ደጋግማ ወትውታታለች፤ የኦርፋን መመለስ በአይኗ ማየቷ፣ ከኑአሚን ጋር ስትኖር ብርቱ የጉልበት ሥራ በሚጠይቅ በእርሻ ወይም በእርባታ ስራ በሚተዳደሩበት ዘመን ያለባል ኑሮዋ፣ እንዲሁም ከኑኃሚን ጋር ብትሄድ ይጠብቅሻል ብላ ኑኃሚን የነገረቻት ኑሮ ራሱ ተመለሺ ብሎ የሚጎተጉቱ ነበሩ። ነገር ግን እርስዋ በዚህ ወሳኝ በሆነ ፈተና ወቅት የሰጠችው ምላሽ አርቆ አሳቢነትና ታላቅ ማስተዋል የሚንጸባረቅበት ተገቢ ምላሽ ነበር። ችኮላ የሌለበት በደንብ በቂ ጊዜ ተወስዶ የታሰበበት ይመስላል። ኑኃሚን ወዳገሯና ወገኖችዋ ብሄድ ባል አታገኚም ትቸገሪያለሽ እያለችኝ ነው። እርሷ ሌላ ልጅ ባይኖራት እስራኤላዊያን ባል የሞተባት ሴት አያገቡም ይሆናል።

ባገሬም እኮ ብዙ በችግር የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ወዳገሬ ብመለስ ኑሮዬ የተቃና እንደሚሆን ማረጋገጫ ወይም ዋስትና የሚሰጠኝ ማን ነው። እስራኤላወዊያን በባህሪያቸው ደህና ሰዎች መሆናቸውን ተጋብተን በነበሩት ልጆችዋና በእርሷ ሕይወት አይቸዋለሁ። በተለይ ስለ አምላካቸው ማንነት የሰማሁት ነገር እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ለብቸኛዋና በዕድሜ ለገፋቸው ምራትዋም በመራራት ኑኃሚን ልጆችዋ ሳሉ በደህና ጊዜዋ አፍቅራኝ ተንከባክባኝ አብሬያት ኖሬያለሁ። እግዚአብሔርም በቤታቸው ደስ አሰኝቶኝ ነበር። አሁን በዕድሜ ስለ ገፍታ ስላረጀች፣ ደከም ባለችበት/መጦር በሚገባትና ችግሯ በተባባሰ ጊዜ ብቻዋን ትቻት እንዴት እሄዳለሁ። በጉዞ ላይ እያለች መንገድ ላይ ብትወድቅ ማን ይደግፋታል ያለች ይመስላል።

አገርዋ ብትደርስም ያለ አንዳች ቤተሰብ በዚህ ዕድሜዋ ለብቻዋ በጣም ስለሚከብዳት የኔ ጉልበት ከእርሷ ስለሚበረታ ሰርቼ እደግፋታለሁ። ስለዚህ ብቸገርም እርሷን፣ ሕዝቧንና ይህን የመሰለ ታላቅና መልካም አምላክ በምንም አይነት ማጣት/መተው የለብኝም ብላ ሕይወትዋና የተሸለ ኑሮ በመሰዋት፣ ቁርጥ ውሳኔ ወስና የሚከተለውን መልስ ለኑኃሚን ሰጠች።

*ሩት 1፡16፣ 17፣ ሩት ግን እንዲህ አለች፤ "ተለይቼሽ እንድቀር ወይም እንድመለስ አትለማመጭኝ፤ ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ፤ በምትኖሪበትም እኖራለሁ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል። [17] በምትሞቺበት እሞታለሁ፤ እዚያው እቀበራለሁ። ከእንግዲህ ሞት ከሚለየን በቀር ብለይሽ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህም የከፋ ያድርግብኝ።"*

ሩት 1፥18፣ "ሩት አብራት ለመሄድ መቊረጧን በተረዳች ጊዜ፣ ኑኃሚን መጐትጐቷን ተወች።"

በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ህዝብ ወገን የሆነችውና እግዚአብሔር ያደረገውን ብዙ ነገር የምታውቀዋ ኑኃሚን ስታማርረው እየሰማች አኔስ እግዚአብሔርን ካልተከተልኩ ሞቼ ልገኝ በማለት ከነኃሚን ጋር ጊዞዋን ቀጠለች።

በሩት 2፡2፣ 8-9፣ ላይ ሩትና ኑኅሚን ቤተልሔም እንደ ደረሱ አንድ ቀን ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ማሳ በወጣችበት ቦዔዝ ከሚባል ዋርሳዋ ሊሆነ ከሚችል መልካም ሰው ጋር ተገኛኝታ በመተዋወቅ ቦኤዝ በመልካም ሁኔታ ተቀበላት፡፡

ሩት 2፡11-12፤ *ቦዔዝም መልሶ እንዲህ አላት፤ "ባልሽ ከሞተ ጀምሮ ለዐማትሽ ያደረግሽላትን ሁሉ፣ አባት እናትሽን እንዲሁም የተወለድሽበትን አገር ትተሽ ቀድሞ ከማታውቂው ሕዝብ ጋር ለመኖር እንዴት እንደመጣሽ ነግረውኛል፡፡ [12] ስላደረግሽው ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋሽን ይክፈልሽ፤ በክንፉ ጥላ ሥር ለመጠለል የመጣሽበት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ብድራትሽን አትረፍርፎ ይመልስልሽ፡፡"*

ሩት 3፡10-11፣ *እርሱም መልሶ እንዲህ አላት፤ "ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር ይባርክሽ፤ ከዚህ በፊት ካደረግሽው ይልቅ ያሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል፤ ባለጠጋም ሆነ ድኻ፣ ወጣት ወንድ ፈልገሽ አልሄድሽምና፡፡ [11] አሁንም ልጄ ሆይ፤ አትፍሪ፤ የምትጠይቂውን ሁሉ አደርግልሻለሁ፤ አንቺ ምግባረ መልካም ሴት መሆንሽንም የአገሬ ሰው ሁሉ ያውቀዋል፡፡"*

ቦኤዝ በምዕራፍ 2 ሩት ለምራትዋ ባደረገችው መልካም ተግባራት፣ የእስራኤልን ሕዝብና የእስራኤላዊያን አምላክ መርጣ መምጣትዋን ስለሰማ በጣም ደስ እንደተሰኘባት ተናግራታል፡፡

በምዕራፍ 3 ደግሞ ከእርሱ ጋር በነበራት ተውውቅ ጅማሬ ስላደረገችው መልካም ተግባር ተደንቆ አሁን ያደረግሽው ቀድሞ ካደረግሽው ይበልታል አላት፡፡ ምግባረ መልካም ሴት መሆንዋን የአገሩ ሕዝብ ሁሉ እንደሚያውቅ በመግለጽ የምትጠይቂውን ሁሉ አድግልሻለሁ ብሏታል፡፡

ሩት 4፡13-15፣ ስለዚህ ቦዔዝ ሩትን ወሰዳት፤ ሚስቱም ሆነች፡፡ ከዚያም ወደ እርሷ ገባ፤ እግዚአብሔር እንድትፀንስ አደረጋት፤ ወንድ ልጅም ወለደች፡፡ [14] ሴቶቹም ኑኃሚንን እንዲህ አሏት፤ "ዛሬ የሚቤዥ ቅርብ የሥጋ ዘመድ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ በመላው እስራኤልም ስሙ ይግነን፡፡ [15] ልጁ ሕይወትሽን ያድሳታል፤ በእርጅና ዘመንሽም ይጦርሻል፤ የምትወድሽና **ከሰባት ወንዶች ልጆች የምትበልጥብሽ ምራትሽ** ወልዳዋለችና፡፡"

**ማጠቃለያ፡-**

***ሀ***. ሩትና ኦርፋ ለሞቱት ባሎቻቸውና ለኑኦሚ መልካም ማድረጋቸው ተመስክሮላቸዋል (2፡8-12)

**ለ**. ሩትና ኦርፋ ባሎቻቸው ከሞቱ በኂላ ለኑኃሚን መልካም ማድረጋቸውን ተመስክሮላቸዋል፡፡ ሩት 2፡11-12፣

**ሐ**. ሩት ከእርሷ ዕድሜ ጋር የሚቀራረብ ወጣት የሆነ እስራኤላዊ ለማግባት በማፈላለግ ፈንታ በማሳው ቃርሚያ ልትቃርም ርህራሄ ያሳያት በዕድሜ ብዙ የሚበልጣት ቦኤዝን ለዋርሳነት በመጠጋትዋ ተወደደላት፤ ቀድሞ ካደረግሽው መልካም ተግባር ይልቅ የአሁኑ ይበልጣል ተባለላት፡፡ ሩት ከጣዖት አምላኪ ቤተሰብ ነው እንጂ፣ በእግዚአብሔር ከሚያምን ቤተሰብ አልተወለደችም፣ አድጋ ባል እስታገባ ድረስም የእግዚአብሔር ቃል አልተማረችም፡፡ እንዴት እንዲህ ዓይነት ቅንና ምግባረ መልካም ሴት እንደሆነች ሁሌ ይገርመኛል፡፡ ሩት 3፡10-11፣

መ. ሩት ብዙዎች እስራኤላዊያን እንኳ ያላከበሩትን እግዚአብሔር መርጣ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል አለች። ሩት 4፡15፣ በእንዲህ ዓይነት ፈታኝ ወቅትና ሂደት ተማምናው የተከተለችው እግዚአብሔር ይገጥምሻል ተብላ ከተነገራት ችግር ተቃራኒ ወደ ሆነ ትዳርና በረከት ሳታስበው እየመራ በአጭር ጊዜ አደረሳት፣ ያላሰበችው መልካም ነገር አዘጋጅቶ ጠበቃት። እንዲህ በተለያየ ውጣ ውረድ ቢያልፉም እግዚአብሔር በመተማመን ጸንተው ለሚከተሉት ያልጠበቁት መልካም ነገር ያዘጋጃል።

ሠ. ሩት በቤተልሔም ሴቶች ከሰባት ወንዶች ልጆች የምትበልጥ ምራት ተባለላት። ለኑሃሚንም ቀኝ እጅ ሆነች። የንጉስ ዳዊት የዘር ሀረግ ውስጥ ገባች። በመልካም ምግባርዋ ስምዋም እስከዛሬ ድረስ ይወደሳል፤ ወደፊትም ገና ብዙ ትውልድ ያወድሳታል። እነዚህ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን ያልነበሩ ሁለቱ ሞአባዊያን ሴቶች እስራኤላዊያንን የሚያስገርም መልካም ሥራ ሰርተው መገኘታቸው በእግዚአብሔር ስም የተጠራ ሕዝብን ልቀው መገኘታቸው የራስን ሕይወት ወደ መገምገም የሚያስኬድ ነው።

ረ. እንደ አግዚአብሔር ታላቅ ነቢያትና ሐዋሪያት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ክፍል መጽሐፈ ሩት በስምዋ ተጠራ፤ መጽሐፉም በዋናነት የእርሷን መልካም አርአያነት ያላቸው ተግባራትና ስለ መልካም ምግባርዋ የሚተርክ ነው።

ሰ. ኃጢአተኛም በኃጢአቱ እግዚአብሔር ሊቀጣው ይችላል። በኃጢአቱ ምክንያት ሰው ሲቀጣ እግዚአብሔርን በማማረር/በማጉረምረም/በመሟገት በኃጢአት ላይ ኃጢአት ከመጨመር በስተቀር መፍትሄ አይገኝም። መፍትሄ የሚገኘው ኃጢአተኝነትን በመቀበልና በንስሀ በመመለስ ነው። ኢዮ 34፡31-33፤

በአንድ የደቡብ ክልለ አካባቢ መብረቅ እንደ አምላክ ቆጥረው የሚያመልኩ ሰዎች አሉ። በዚያ አካባቢ መብረቅ የአንድን ሰው ቤት ማቃጠል ከጀመረ የቤቱ ባለቤቶችም ሆነ ጎረቤቶች በሚቃጠለው ቤት አጠገብ በመሰባሰብ ቆመው ያያሉ እንጂ እሳቱን ለማጥፋት ሙከራ አያደርጉም። ምክንያቱም መቃጠል የጀመረውን ቤት ለማጥፋት ከሞከሩ መብረቅን ያስቆጣና እሳቱ ይጋጋላል፣ ደግሞም መብረቅ ተቆጥቶ ሌላ ተጨማሪ ቤት ያቃጥላል ብለው ስለሚፈሩ ነው። ከዚህም ሌላ መብረቅ ቤት አቃጠለ እየተባባሉ አይነጋገሩም፣ መብረቅ ማንኛውም የቤት እንስሳም ሆነ ቤትና ንብረት ቢያጠፋም አበጀ ይባላል እንጂ አጠፋ አይባልም። ምክንያቱም መብረቅ በጣም ስለሚፈራ ይከበራል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን አምላኩን እንደዚህ በማክበር ፈንታ ስለ ተላመደው የድፍረት ንግግር ስለሚናገር መታረም ያለበት ነው።

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2019 ዓ.ም.